# ለኢትዮጲያ ና ለህዝቧ የሚበጀው ነገር (ክፍል ፫)

*ከሙሉቀን ገበየው*

በክፍል ፪ ጽሑፌ ከ27 አመታት የአፈናና አስከፊ አገዛዝ ቦኋላ የሽግግሩን ሂደቱን በመንግስትነት የሚመሩት ሙሉ በሙሉ ካልፈርሰው አገዛዝ የተወከሉ "የለውጥ ፈላጊ" መሪዎችና በተፈጠርው ለውጥ የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማራመድ በተሰባሰቡ ወገኖች በኩል የተዘነጋውን ወሳኝ የሽግግር ወቅት ስራና ወደፊት ሊያጤኑት የሚገባቸውን መሰርታዊ የሃገርችንና ህዝብ ችግር መፍቻ መሳሪያዎችን በማብራራት ነበር። በተለይ የይቅርታ እርቅ ና የህዝብ መግባባት መድርኮችን ባስቸኳይ አስፍላጊንትና የከፋፍልህ ግዛው ፖሊስን ማዳከምና ማጥፋት ወሳኝ ተግባርቶች መሆናቸውን፤ በተለይም ሊከትል የሚችለውን ሌሎች የለወጥ ስራ እንዴት እንድሚያቀለው በመግለጽ ነበር። የሽግግሩ መንግስት መሪዎችን እርጋታንና ማስተዋልን ትኩርትን እንዲያካብቱ በመምከር በተለይም ፋይዳ ያለው ፍኖት- ካርታ በግልጽ በመንደፍ የለውጡን ምህዋር ማሳየት እንዳለባቸው ተገልጿል።

በክፍል ፪ መሰርታዊ አገራዊ መግባባት ሳይደርግ ለምርጫው መቻኮል ትርፉ ኪሳራ መሆኑን፤ እንዲሁም ወያኔ ላገዘዙ ያመቸው ዘንድ በላያችን ላይ የተከለው ህዝብ ያልመከረበትን ህገ- መንግስት ወደፊት የጥፋት ምንጭ ስለሚሆንብን መምርመር እንዳለብን ፤ካስፈለገም አዲስ ማርቀቅ ወይም ማሻሻል እንደሚያስፈልግ፤ በጎሳ ላይ የተመሰርተ ፖለቲካ ወይም ስርአት አግላይና የሚለያይ መሆኑን አጽኖ በመስጠት በጎሳ መድራጅትን ጎጂ መሆኑን፤ ህዝቡን አስተምረን በህግ ማስቀርትና በዜግነት የሰው መስርትነት ላይ የተነሳ ስርአተ-መንግስት እንድሚያስፈልገን በመግልጽ ነበር። ወያኔው አስምሮ የሰጠንን ህዝብ ያልመከረበትን የክልል ወሰን አጥፈተን፤ በመከርነብት አዲስ የፌድራል መንግሳታት ሀገርና ህዝብን የሚያሳድጉ በሚጠቅም መልክ የተዝጋጁ፤ ህዝቡ ለስልጣን ቅርብ እንድሆን የሚያመቻቹ፤ እንዲሁም እንድ ኢትዮጵያ ላለ ታሪካዊና ታላቅ አገርና ህዝብ የአገራችን አስተዳድር ፕሬዝዳንታዊ እንዲሆንና ክፍለ ሃገራትም (federal regional state) እንዲሁም ትላልቅ ከተሞች በህዝብ በሚምርጡ አስተዳድሪዎችና ከንቲባዎች ( Governor and mayor ) ቢተዳደሩ መልካም እንድሆነና ፤ ባንድ ዋና ከተማ ላይ ከምንረባረብ፣ ወደፊት የተለያዩ ከተሞች ን እንዲመስርቱና ያሉትንም እንድስፋፉ ቢድርገ የተሻለ መሆኑን በመገለጽ ነበር።

በዚህኛው ጽሁፌ የመምለከትው ሁሌም የምንሸሸውና የማንነጋግርበት፤ ነገር ግን ሊሁን የሚችል ትልቅ አደጋን መመልከት ነው። ወያኔው ለ 27 አመት ባቀነቀነው ብልሹ ዘርን መሰርት ያደርገ ፖለቲካ ህዝቡ እክ እንትፍ ቢያደርገውም ስርአቱ ሙሉ ለሙሉ ስላልፈርሰና ከውስጡም በመጡ "የለውጥ ፈላጊዎች" ከነ እድፋቸው የሽግግሩን ሂደት በመሪንት በማያዛቸው፤ በተለይ ደግሞ የዘር ፖለቲካን የሚያቀነቅኑ ከወያኔው ጋ ተመሳሳይ አቋም የነበራቸው ነገር ግን ወያኔ ስልጣን ሳያጋራ ያባረራቸው የጎሳ አክራሪ የፖለቲካ ድሪቶ ፓርቲዎች ሀገር ቤት ከንግሳንግሳቸው ያለ ስርአተና ህግ እንዲገቡና እንድፈንጥዙ በመደርጋቸው እንዲህም በጥላቻና ልይኑት ላይ ያተኮረ ግማሽ እውነት ይዘው በተጋነነ ትርከት ህዝቡ ወስጥ ከነሚድያቸው እንዲገቡ ስለፈቀደና፤ ህዝቡንም በፕሮፓጋንዳ ሰመምን ውስጥ በማስገብታቸው፣ ህዝቡ ሲታገለው የነበርውን የ 27 አመታት የዘር ፖለቲካ ፈተና በሌላ መልክ ከሽነው በማቀርብቻው፤ እነዚ ሃይሎችን የሚያስታግስ ተመሳሳይ ሰላማዊ ጸረ-ዘር ፖልቲከኛ ስብስብን እድል ባለማግኘቱና ባለመበርታቱ ህዝቡን ወደተሳሳተ መንግድ ሊመሩት ችለዋል። ነግር ገን ምን ያህል እንድሚያራምዳቸ የምናወቀው ወደፊት ነው።

ባንድ በኩል ይቅርታና እርቅ እንዲሁም የህዝብ መቀራረብ እንዳይደርገ እይከለከሉ፣ በሌላ በኩል የጥላቻ ና የልዩነት መዝሙር እየዘፈኑ፣ በማስፈራርት፣ በመሳርያ ሀይል አገር እይዘረፉና እንዳልተገራ ወይፈን እይፈንጩ ከልካይ በመጣታቱ ( ህግን ማስከብር ባልመቻሉ) አገራችን እንዚህን የስልጣን ጥም ባሰከርቸው ሰዎች ወይም ስብስቦች ህልም ና ቅዠት ውስጥ ልትገባ በቅታለች። ይህም ወያኔ ህዝብን ሳያማክር ለአገዛዙ በሚያመቸው ከፋፍለህ ግዛው መልክ በሰፍርላቸውና ባሰመረላቸው ድንበር መሰርት በማድርግ የመገንጠል ጥያቄ ሊመጣ ይችላል። ችግሩ መገንጠሉ ሳይሆን በህዝብ ፈቃድ ላይ የተመሰርተ ሳይሆን ለስልጣን፣ ለታሪክ ሽሚያ እንዲሁም ሃብት ለማካበቻ የሚጠቅማቸውን ጥቂት አለን አለን የሚሉ የጎሳ ፖለቲካ ነጋዴዎችን መሆኑ ነው። ችግር ቢፈጠርና ከቁጥጥርቸው ውጪ ቢሆን ህዝቡን አጋልጠዉ እንርሱ የያዙትን የአሚሪካን ፤ የአውሮፓ እንዲሁም ካናዳ ና አውስትርሊያ ፓስፖርታቸውን ይዘው ከነቤተሰቦቻቸው ይፈርጠጣሉ። የእሳት ማገዶ የሚሆነው ግን ሰፊው ህዝብ ነው።

በህግም ይሁን በጉልበት የሚፈልጉትን አገር የመገንጠልና መንግስት የመሆን ህልም ወይም ቅዥት እንድመልከተው። እንኳን የተለያዩ መንግስት ሆነው ባንድ ፌዴራላዊ መንግስት ጥላ ስር ውስጥ እንኳን ሁነው በመሬትና ወሰን ይገባኛል ስንት እልቂትና ህዝብ እንድተፈናቀለ የቅርብ ግዜ ትውስታቸን ነው።

እነ ኦነግና አጫፋሪ አክቲቭስቶቹ የሚምኝዋትን ኦሮሚያ የምትባል ሃገር ወያኔ በሰፍረላት ድንበር ወስን ተግነጥላ መንግስት ትሁን እንበል። በምስርቅ በኩል ከ1000 ኪሎሚትር በላይ ከኢትዮጵያ ሶማሌ ጋ ትዋሰንላች። ይህ በህዝብ ፈቃድ ሳይሆን በወያኔው ለአገዛዝ ያመቸው ዘንድ ያሰመርው የድንበር መስመር የሃስት ስለሆነ ወደ ማያባራ ጦረነትና መፈናቃል በዚያ በኩል ይፈጸማል። በሰሜን በኩል ከአማራ ከሚባል መንግስት ጋ ደግሞ ብዙ የሚያጋጭ ድንበርና የታሪክ የፕሮፕጋንዳ ቁርሾ ስላለ ሌላ ጦርነት ይጠብቃታል፤ በምራብ በኩል ከደቡብ ህዝቦች በተለይም በጉጂና ጌድዎ እንዲሁም በሌሎችም ጋ የወሰንና የተፈጥሮ ሃብት ሽሚያ ጦርነት ይፈጥራል።

ኦሮሚያ ውስጥ ከ15 ሚሊዮን በላይ የሌላ ጎሳ ተወላጅ ኢትዮጲያን ይኖራሉ። እንዚህም ዝም ብለው እጃቸውን አጣጥፈው በሚመስረተው የጎስኛ መንግስት ጋ ለመኖር ይቸገራሉ። ወይ ሁለተኛ ዜጋ ሁኑ ይባላሉ ወይም ኦሮሚያን ልቀቁ ተብለው ሌለ ጦርነትና እሳት ይፈጠራል። ሌላው አዲስ አበባ የሁሉ ኢትዮጲያዊ ዜጋ መኖርያን በህዝብ ሃብት የተመሰርተችን ከተማ ራሱን የቻለ ትልቅ ችግር ይሆናል። ባጠቃላይ ማስርጃዎቹ የሚያሳዩት ትልቅ የጦርነት ቀጠና የሆንች ኦሮሚያ ስትሆን የርስ በርስ ጦርነት አውድማ ትሆንና ሶማሊያ፣ ሶርያ የቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ አይንት እልቂትና እጣ ይሆናል። በዚያን ግዜ ዋና ዋና አጋፍሪዎቹ ህዝቡን ማገደው ወደ አሜሪካና ካናዳ ፣አውሮፓ አውስትራልያ ይፈረጥጣሉ።

ይህ ጥፋት የሚደርሰው በኦርሚያ መገንጠል ብቻ አይደለም። አማራ የሚባል አገርም ልገንጠል ቢል ተመሳሳይ እጣ ነው የሚደርሰው። ትግራይም ልገንጥል ብትል አሁን ወያኔ ከሌሎች ቦታዎች ነጥቆ የወስዳቸውን መሪቶች ይዞ ልገንጥል ቢል በደቡብ አማራ ከሚባል መንግስት ጋ፣ በምስራቅ ከአፋር ከሚባል መንግስት ጋ፣ በሰሜን ከኤርትራ ጋ ስትዋጋ መንሮዋ ነው። ይህም ብቻ አይደለም ፖሊትከኞቹ ማየት እና መስማት የማይፈልጉት ሀቅ ግን አብዝኛው ኢትዮጲያውያን በደም የተቀላቀለ መሆኑን ነው። በተለይ መሃል አገር ያለው ኦሮሞና አማራ፣ በሰሜን ትግራይና አማራ፣ በምስራቅ ሱማሌና ኦሮሞ እንዲሁም በሌሎች ቦታዎች ሁሉ የተዛመደ ህዝብ ነው።

የአገራችን ህዝብ በነዚህ የፖለቲካ ነጋዴዎች የተሸረበውን ሴራ በድንብ ማጤን ይኖርበታል። ምልክቶቹን በመላው አገርችን በተለይም በኦርሚያና ኢትዮ ሶማልያ ድንበር፣ በጊድዮና በጉጂ፣ በሲዳማና ወላይታ፣ በአሶሳ አከባቢ፣ በቢንሻንጉል እንዲሁም በሰሜን አማራና ትግራይ ህዝቦች ላይ የደርሰውን የቅርብ ግዜ እልቂቶችና ጥፋቶችን ማስተዋል ይገባል።

እነዚ በጎሳ የመገንጠል የሚያቀነቅኑ የፖለቲካ ነግዴውች በዚያ ብቻ አይበቁም። ቢቻልቸው የገንጥሉትን ሃገር ደሞ በሃይማኖት ሊገንጥሉትና ሊከፋፍሉት መጣራቸው አይቀርም። ኦርሚያ ብቻ ብለው አይቆሙም። እንደ ገና ባአውራጃ የሀረር፣የወለጋ፣ የሸዋ የቦረና የሚል ሌላ አባዜውች ይገባሉ። አማራን እንገንጥል የሚሉ ደግሞ ጎጃም፣ ጎንደር፣ ሸዋ፣ ወሎ ማለታቸው አይቀርም።

እውነቱ እንግዲ ይሄ ነው።እንገንጠላለን ብለው የሚያስፈራሩትም የሚገጥምቸው ለምለምና ሰላም የሞላበት አገር ሳይሆን እሳትና ሞት ነው። ይህ ማስፈራርታቸውንም ሌለው ህዝብ አውቆ አደባቸውን እንዲገዙ፣ ህዝቡንም ለአሳት እንዳይጥሉ በመነጋገርና በመከራከር ይሄ የሽግግሩ መንግስት የሰጣቸውን ከልካይ የለብኝም ሜዳ መስምር ማስያዝ ያስፈልጋል።

እንዚ የፖሉቲካ ነጋዴዎች የሚፈልጉትን አገር መግነጠል ሲራ ሳይሳካልቸው የሚቀር መስሎ ሲታያቸው ደግሞ ሌላወን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ላይ የበላይ ሁነው እነሱ በሚዘውርዋት በስም ብቻ ኢትዮጲያ የምትባል አገር መሪዎች መሆንንም ያልማሉ። ወያኔው ከፋፍሎ ለ27 አመታት እንደገዛን ሁሉ እንርሱም ድርሻው አሁን የኛ ነው በሚል ስሌት ይህን ምስኪን ህዝብ ለአዲስ የመከራ አገዛዝ ያዘጋጁታል።

27 አመታት ሙሉ ህዝቡ ያለመታከት የሞተለትና የደከሙብትን ሰላማዊ ትግል፡ ባለቀ ሰአት ተቀላቅለው፤ የነበሩበትን እስከፊ ሰርአት ሙሉ ለሙሉ ሳይጠፉ፣ ከተቻለ ራሳቸውንና የአዲሲቷ ኢትዮጲያ ገዥዎች ለማድርግ፤ ካልተቻለም እንደገና ራሳቸውን ከመጡበትት ጎሳ ፖለቲካ ጫካ ውስጥ ገብተው ባክራሪዎቹ ይዘመር የነበረውን ሁሉ፣ ቀድሞ አደራጊና አስፍጻሚ የመሆን ሽኩቻ ውስጥ ገብተዋል። ለእወነተኛ አገራዊ ለውጥ የተነሱትን ሰዎች ከመካከላቸው እያራቁ፣ እያባረሩ ያአክራሪዎችን አጀንዳ ና ጥፋት ፈጻሚ በመሆን በመጀምርያ በድብቅ ቦኋላም በግልጽ ሴራ ላይ ተስማርተውል።

የጎሳ ፖለቲካና የመገንጠል አባዜ የያዛቸው የፖለቲካ ነጋዴዎቹ አዲስ ጥናትና ቀመር በድንብ አዘጋጅተው ስለመጡ፣ የኢትዩጵያ ህዝብ እስኪነቃ ድርስ ብዙ ጥፋት ያደርሳሉ። ከሚጠቀሙበት ዘዴ አንዱ በሚከተለው ምሳሌ ይገለጻል። አላማቸው በሞሶቡ ውስጥ ካለው ሙሉሙል ዳቦውች አንዱን ማግኘት ቢሆንም ፡ አንዱን ሙሉምል ይሰጠኝ ብለው ሳይሆን የሚጠይቁት ሞሲቡ ይገባኛል ብለው የቤቱን ባለቤት ይሞግቱታል። ሰውየውም ተድናግጦ አይ ሞሶቡን ሳይሆን ባይሆን አምስት ሙሉሙል ነው የምስጥህ ይለውና አምስቱን ሙልሙል ያስርከባል። የአክራሪዎች የፖለቲካ ነጋዲዎች አሁን ያለውን የሽግግር መንግስት በዚህ መልክ እየጠይቁት አመራሮችን ግራ እያጋቡ ካሰቡት በላይ ይሰበስባሉ። ረጋ ብሎ ላስተዋለ አሁን ጎልተው የሚታዩት የፖለቲካ አጀንዳዎች በብዛት የአገራችን ህዝብ ችገር፣ የደከመበት፣ የታገለበትን አጀንዳ ሳይሆን እንዚህ አክራሪዎች የሚጠይቁትና የሚሰብሰቡትን ነው።

(ክፍል ፬ ይቀጥላል)።